

አይፐሲዜ
እና ሌሎች መጎች
ዘነበ ወላ

‹አይ ፐሲዜ› እና ሌሎች ወጎች...



ዘነበ ወላ

2014 ዓ.ም

‹ለይ ፕሲዜ› እና ሌሎች ወገች...

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያ ዕትም ሐምሌ 2014 ዓ.ም

ዘነበ ወለ ወጋ

ኢሜይል፡ znebwol@yahoo.com

znebwola@gmail.com

የሽፋን ቅንብር፡- ፍስሀ መዓዛ

09 24 54 12 97

የኮምፒተር ፅሁፍ ፡- ቅድስት የሺጥላ

0911 87 33 63

መታሰቢያ

ለጥምቀት አስማማው

ለእስክንድር ታይሉ

ለብሌን ታይለሚካኤል

ከጓደኝነት በተጨማሪ ለሥራዬ መቃናት የበኩላቸውን አድርገውልኛል፤ እኔም ለባልንጀራነታችን መታሰቢያ ትሆን ዘንድ ይህቺን ሥራዬን በታላቅ አክብሮት አበርክቻለሁ።

ሕግ ሲለላ የሠው ልጅ ጨካኝ እንደሆነ ይህ ዘመን አሳይቶናል ። በዚህ ቅጥ ያጣ የጭካኔ ወቅት በአራቱም ማእዘን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ህይወታቸውን አጥተዋል ። ችርነቱ የማይጓደል አምላክ ነብሳቸውን በገነት ያኑርልን እያልኩ ይህቺ ሥራዬ ለሠማእቱ ማስታወሻ ትሆን ዘንድ አበርክቻታለሁ ። በሌላ በኩል ደግሞ ዘመኑ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተለምር የተሰራበት ነው ። ታላቁ የህዳሴ ግድብ አውራው እና ተጠቃሹ ነው ። በዚያ ንዳድ የአየር ንብረት ውስጥ ሆነው ታላቅ ተግባራቸውን የሚያከናውኑ ወገኖቻችንን እና አጋሮቻችንን በፍቅር እያሰብኩ ይህቺ መጽሐፍ መታሰቢያ ትሆናቸው ዘንድ ሳበረክትላቸው በታላቅ ደስታ ነው ።

" ሠላም በምድራችን ላይ ይስፈን !"

ምስጋና

ይህንን ሥራዬን አሰባስቤ ለአንባቢያን እንዳቀርብ ያተጉኝን ወዳጆቼን መግቢያዬ ላይ ገልጫለሁ። ሥራው ከተጀመረ በኋላ ወዳጄ ባዩልኝ አያሌው እና ቅድስት የሺጥላ በእንዲህ መልኩ በምልአት እንዳስጠርዘው ሙያዊ አስተዋፅኦ አድርገውልኛል። ለዚህ ቸርነታቸው እነዚህን ባልንጀሮቼን ሳመሰግን ከልብ ነው። «ከሰው ስህተት ከብረት ዝገት» እንዲሉት አንባቢው ግድፈት ከገጠመው እኔው ፀሐፊ፣ አሰባሳቢ፣ አራሚ፣ አሳታሚ ሆኜ የሠራሁት ስለሆነ በሥራው ጫና እንጂ በዋል ፈሰስነት የተፈጠረ አለመሆኑን አውቆ ግድፈቱን አርሞ እንደሚያነበኝ ከልብ እተማመናለሁ። ካጠፋሁም ከወዲሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

መልካም ንባብ

ዘ.ወ

ማውጫ

ጥበብና ጠቢባን

ሴቶችና ጋሼ ስብሐት በድርብቡ 10
ብዕር ማሚሻ 20
ሕያው ደራሲ 30
ደራሲና ዲሲፕሊን 43
በሦስት ቋንቋ ደራሲው 51
የጥበበ ቃላት ተመራማሪው 62
50 መጻሕፍትን በ 44 ዓመታት 71
አሐዱ ሳቡሬ 84
ኩርኮራ 92
ፍራንሲስ ፋልሴቶ 109

ማሕበራዊ

ተግባራዊነትን የምንዋሃደው መቼ ይሆን? 121
ጨዋ ማጅራት መቺዎች 131
ተፈጥሮን አፍቃሪ 137
ትዕግስትና ውጤት 158
ሰለሞን ‹አስትሮሎጂ› 163
በብዕር ተፋላሚው ጋዜጠኛ 173
ድንቅ ሰው! 200
‹‹ሳይለምኑኝ!›› 212

ሀገርና ፖለቲካ

‹ላይ ፐሲዜ?› 228
አፍሪቃዊነት 235
አንድ ለአንድ 246
የታጋዩ ማስታወሻ 282

የተከበራችሁ አንባቢያን

ከ29 ዓመታት በፊት እኔና ጋሼ ስብሐትለአብ ስለ ድርሰትና ደራሲያን በለፈው ስንጨዋወት፣ ሥራዎቻቸው በመጽሔቶች ላይ ለህትመት በቅተው ለዳግም ንባብ ስለበቁ ደራሲያን በአያሌው ማውጋታችንን አስታውሳለሁ። ከምጠቅሰው አንዱ ቻርልስ ዲከንስ (1812-1870) ነው። ዲከንስ ሥራዎቹ በመጽሔቶች ላይ መጀመሪያ ለህትመት ይበቃሉ። እነዚህ ሥራዎች ትረካቸው እንደተጠናቀቀ፣ ይሰበሰቡና በመጽሐፍ ይታተማሉ። ይህ የእኔና የጋሼ ስብሐት ለአብ ውይይት ‹‹ማስታወሻ›› በሚል መጽሐፍ ለህትመት በቅቶ፣ በአገራችን አዲሱ ትውልድ አንብቦ አንዳንዶች ይረባል ብለው ያሰቡትን ሥራዎቻቸውን ከየመጽሔቱና ጋዜጣው ላይ አሰባስበው ለሕትመት ሲያበቁ ላይ፣ ምንአልባት የእኔና የጋሼ ስብሐት ለአብ ውይይት መንገዱን መርቷቸው ይሆን? ስል አብሰለስላለሁ።

ነብሱን ይማረውና ወዳጄ አብደላ እዝራ በኤፍ. ኤም 97.1 በአዲስ ዜማ አወጋቸው የነበሩትን ወጎች አድምጧቸው ኖሮ፣ የመጨረሻችን በሆነችው አንዷ ዕለት ብሔራዊ ቴአትር መናፈሻው ውስጥ ተገናኝተን ይህንን የሬዲዮ ወጌን እንዳስጠርዘው አሳሰበኝ። ‹‹ማለፊያ እሞክራለሁ!›› ነበር ያልኩት። በወቅቱ ሕሊናዬ ውስጥ የተከሰተው በአዲስ ሃሳብ መፃፍ ነበር። እንደወጠንኩትም ‹መልህቅ› ጻፍኩ። ክፍል ሁለቱንም የመጨረሻውን ምዕራፍ አጠናቀቅኩ። በተከታይም እነዚህ ወጎች ላይ አተኮርኩ።

እታፍዘር ማተሚያ ቤት ብቅ ብዬ በአዲስ ሥራዬ ላይ ከኃላፊዎቹ ጋር ስወያይ ዲዛይነሩ ፍስሀ መአዛ ‹‹ቀጣይ ሥራህን የመጽሐፉን ሽፋን ለምን እኔ አልሰራልህም? በወግ ስብስብ ብትመጣ ደግሞ አሪፍ ነው›› አለኝ።

እዚያው ጭውውት ላይ ‹አይፐሲዜ› ስለተባለው ወግ አወራሁት። ሀሳቡን ወዶት ድንቅ ሽፋን ሰርቶ በቀጣዩ ቀጠሯችን አሳየኝ፤ ይህም ሥራውን ወድጄው ፅሁፎቹን ከያለበት ፈልጎ ማሰባሰቡን ሥራዬ ብዬ ያዝኩት።

እዚህ ጥራዝ ውስጥ የምታገኟቸው ወጎች አዳዲሶችም ከዓመታት በፊት የፃፍኳቸውም ናቸው። ድሮ የፃፍኳቸው የሚያዝናኑ የሰዎችን እምነት አመለካከት የሚያስገነዝቡ ሆነው ለተደራሲያን አንድ ዓይነት ግንዛቤን ያስጨብጣሉ ብዬ ያሰብኳቸውን አካትቻለሁ። በህይወት ጉዞዬ ላይ ያናገርኳቸው አንጋፋ ደራሲያንን ያደረግነውን ቃለ ምልልስ በዚሁ ጥራዝ እንዲካተቱ አድርጌያለሁ። የጎልማሳውን ደራሲ የወዳጄ ሠርቅ ዳ. ቃለ ምልልስን እዚህ ውስጥ አካትቻለሁ። አንድም ያወጋነው አሪፍ ስለሆነ፣ ሁለትም እርሱንም ከዚያ በኋላ አይቼው ስለማላውቅ ወዳጄ የት ነህ? ለማለት ነው።

አንጋፋዎቹ ሀዲስ አለማየሁ፣ ስብሐትለአብ ገ/እግዚአብሔር፣ ሣህለ ሥላሴ ብርሃነማርያም፣ አስፋው ዳምጤን፣ ማሞ ውድነህን፣ አሀዱ ሳቡሬ ያደረግኳቸውን ቃለ ምልልሶች እዚህ ጥራዝ ውስጥ ታገኙታላችሁ።

ጉልምስና እየመጣሁ ነው ሲለኝ እርባና አላቸው ብዬ በሌላ መጻሕፍት መድብል ውስጥ የተካተቱ ሥራዎቼም፣ ወዲህ አምጥቼ አንድ ላይ ተጠርዘው እንዲቀመጡ አድርጌያለሁ። የምጠቅሰው ስለ አሰፋ ጎሣዬ የፃፍኩትን (ድንቅና ዘላለማዊ ሰው) አድርጌ ስለማስበው የድሮው እንዲያስበው፣ አዲሱ ትውልድም እንዲያውቀው አሴን አካትቻለሁ።

የሚያስገርሙ ጓደኞች ነበሩኝ፤ ነበሩኝ ልበል ሁለቱም አልፈዋል። በተለየ የህይወት አተያያቸው ስለነዚህ ጓደኞቼ ቀደም ብዬ ጋዜጣ ላይ ፅፌ ነበር። አንደኛው ሰለሞን ታደሰ ጎሣ፣ ሲሆን ሌላው ዮሴፍ ተስፋሚካኤል ነው። ምን አሉኝ? ከእነርሱ ጋር ከተለያየን በኋላ ምን ተሰማኝ? ይህም የወጎቹ አካል ሆኖ ታገኙታላችሁ።

ወጣት ደራሲያንን በማበረታታት ለእኔ ተጠቃሽዋ ስንዱ አበበ ነች። ባህር ተሻገረች፣ በጣም ራቀች፣ በዚህም መነፋፈቁ የሆድ የሆድን ማውራቱ ቀረ፤ ትዝታ ሲመጣ ስለሷ የሚሰማኝን፣ በእኔ አይን ስንዱን ሳያት የሚያሳይ ወግ አለ። ስለ እርሷ ስፅፍ እግረ መንገዴንም አመሰግንሻለሁ እንደ ማለት ነው።

በአስራ ዘጠኝ ዘጠናዎቹ ውስጥ አገራችን በርካታ ድንቅ በብዕር ተፋላሚ ጋዜጠኞች ፈጥራ ነበር። በዚህም ሌብነቱን፣ የፖለቲካ ሸፍጡን አቅማቸው በፈቀደ መጠን ተከላክለውልናል። የዚያኑ ያህል የእነሱ መመናመን ሙስናውን እንደ ሰደድ እሳት አቀጣጠለው። ከእነዚህ ተፋላሚዎቻችን ውስጥ አንደኛው በፍቃዱ ሞረዳ ነበር። በፍቃዱን አምና ለአገሩ ምድር በቅቶ የነበረበትን ሁኔታ አነጋግሬዋለሁ። እርሱም ሕይወቱን ያወጋናል።

የኢትዮጵያን ዘመናዊ ሙዚቃ ባህር ማዶ ተሻግሮ የሌላው ዓለም ህዝብ እንዲያደምጠው ፍራንሲስ ፋልሴቶ ማለፊያ ድልድይ ፈጥሮለታል። ከእሱም ጋር ከዓመታት በፊት አውግተን ነበር። ይህንኑ ወጋችንን እዚህ ጥራዝ ውስጥ እንዲካተት አድርጌያለሁ።

በርካታ አዳዲስ ሃሳቦች በሥራዬ ውስጥ አካትቻለሁ። ዝርክርኩ የኒካራጓ ኮሙኒስት ፓርቲ ሊቀመንበር ሆዜ ሆንዳ ማስታወሻ የመያዝ ልምድ አለው ይህቺ በመረጃ የታመቀች ማስታወሻ በምዕራብ ደህንነቶች ተመነተፈች። ምላሹን ከመጽሐፍዋ።

አፍሪቃዊነትን በዚህ ሥራዬ ፈትሻለሁ በንድፈ ሀሳብ ተደንግጋ ከአንድ ምዕተ ዓመት ፈቅ ያለውን ዘመናዊ ትምህርታችንንም ፈትሼ ተግባራዊ መሆን የምንችለው መቼ ነው? ስል እጠይቃለሁ።

አገራችን ያለችበት ሁኔታ እንደ ዜጋ እንቅልፍ ከሚነሱኝ ጉዳዮች መካከል አውራው ነው። ይህንን አስመልክቼ በአሁኑ ሰዓት የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንት ለሆኑት ጆ ባይደን አንድ ፅሁፍ መፃፍ አሰኘኝ። መጀመሪያ ‹ፌስቡክ› ገፄ ላይ ልጽፍ አሰብኩ። ይሁን እንጂ አላደረግኩትም፣ ምክንያቱም ሀሳቡ ሰፊ ሆኖ በገፁ ላይ በጥቂት አንቀፅ መግለፅ አይቻልም። ለጋዜጣ ዝግጅት ክፍል መፃፍ ፈለግኩ፣ ይህም ከጉዳዩ ስፋት አኳያ የአንጀቴን የሚያደርስልኝ አልመሰለኝም። የምመረምረው ከአንድ ምዓተ ዓመት በላይ የሆነ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ስለሆነ ይህንን ሀሳብ ‹አንድ ለአንድ› በሚል ርዕስ ፅፌ ለጆ ባይደን በግል ልልክላቸው፣ እናንተም ሀሳቤን እንድትጋሩኝ አንዱ ወግ አድርጌ አስጠርዤዋለሁ። አንብቦ ሀሳቤን መገብየቱን ለእናንተው አተመ ሁ :


‹‹ለለሜሪካን ፕሬዚዳንት?››

‹‹ለምን ለለሜሪካን ፕሬዚዳንት ጀ ባይደን ደብዳቤ ጻፍኩላቸው›› ስላችሁ እንዳንድ ሰምች ካኪ ለብሼ ሲያዩ ቀላል ሰው እመስላቸዋለሁ። እኔ የሰውዬው ልጅ እንዲሁም የሴትዮዋ ማን እንደሆንኩ ታያላችሁ።

የመድበሉ ርዕስ ‹ለይ ፕሲዜ› ነው። ‹ለይ ፕሲዜ› ቃሉ የጋሞ ነው፤ ትርጓሜውም ምን ይረባል? ምን ያድናል?፣ ምን ይፈይዳል? እንዲሉት ይሆናል። ቃሉ በሚነሳው ጉዳይ ላይ ንቀትን ለማሳየት የሚጠቀሙበት ነው። በዚህ ቃል መነሻነት የፃፍኩት ወግ አለ። የእኛን ኢትዮጵያውያንን ምስል፣ አስተሳሰብ ታሳይልኛለች። ወይም ሌላ ምስል ይታያችሁ ይሆናል። ለማንኛውም እስኪ አንብቡኝ። መልካም ንባብ!

ዘ. ወ

አ.አ



ፎቶ በአክሊሉ ገብረመድህን

ዘነበ ወላ፤ የምር ደራሲ፤ ብርቱ የሥነጽሑፍ ሰው ነው። ሳይታክት ዘወትር ያነባል፤ ጠይቆ በአንክሮ ያዳምጣል፤ ሰነዶችን ሳይመረምር ቢሉ በበቂ ሳያጠና የሚጽፍበት ርዕሰ ጉዳይ የለም ብል እያጋነንኩ አይደለም። ዘነበ ድንቅ ተራኪ ነው። ተራ እና ተርታ የሚባለው ጉዳይ እንኳን በዘነበ ብዕር ሲቀርብ ጣዕምና ለዛው ላሳር ነው። ዘነበ በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ውስጥ በድንቅ ተራኪነታቸው ከማደንቃቸው (በድንቅ ተራኪነታቸው ነው ያልኩት) እጅግ ጥቂት ደራሲያን መካከል ከግንባር ቀደሞቹ የምጠቅሰው ነው። ይህንንም ምልከታዬን ሥራዎቹን ያነበቡ የሚጋሩት ይመስለኛል።

"ሕይወት በባህር ውስጥ" ብሎ በሰየመው የበኩር ሥራው፤ ከባህሩ አፋፍ እስከ ጥልቁ የሚገኙትን ፍጥረታት ከሊቅ እስከ ደቂቅ በድንቅና ቀላል አቀራረብ እየተዝናናን እና እየተገረምን እንድናውቃቸው አድርጎናል። በ"ልጅነት"፤ ኖረን ያለፍነውን ልጅነታችንን ከትቦ፤ የልቦለዶቹ ገጸባርያት የሆንን እስኪመስለን ድረስ ቀልባችንን ቀይዶ አስደምሞናል። በ"መልሕቅ" በድንቅ አተራረክ መርከበኛን እና መርከበኝነትን፤ የባህርን ሕይወት ከመቃኘት አልፈን፤ በእዛ አንድን ሀገር ወደ ሁለት ሀገር በከፈለ፤ የብዙ ኢትዮጵያውያንን ነፍስ በበላ አውዳሚ ጦርነት ውስጥ እንደንጋት ኮከብ እያበራ ስለሚንቀለቀል ፍቅር አስቃኝቶናል። የታላቁን ደራሲያችንን (መምህሬም ነው ይለዋል) የስብሐት ገብረ እግዚአብሔርን ንባቡን፤ ምልከታውን፤ ፍልስፍናውን፤ ሕይወቱን እና እውነቱን የከተበበትን "ማስታወሻ"፤ የብርቱውን የአካባቢ ጥበቃ ተሟጋች፤ ተመራማሪ እና ድንቅ መምህር ሕይወትና ተጋድሎ የቀነበበባቸው መንታ ሥራዎች ("የምድራችን ጀግና"ን እና "ኢትዮጵያዊው ሳይንቲስት") የዘነበን ብርቱ ደራሲነት ያለነጋሪ የሚመሰክሩ ናቸው።

"አይፐሲዜ" በዓይነቱና አቀራረቡ ከቀዳሚዎቹ የደራሲው ሥራዎች ይለያል። "አይፐሲዜ" ታላላቅ ሐሳቦችን እና ምልከታዎችን ያቋቱ፤ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን ሆነው በምልዐት የቆሙ ሥራዎች በአንድ የታደሙበት ሥራ ነው። ከኪነጥበባዊ እስከ ማህበራዊ ጉዳዮች፤ ከሀገራዊ ጉዳዮች እስከ ድንቅ ግለሰቦች የሕይወት ምልከታዎች እና የደራሲው ትዝብቶች በድንቅ አተራረክ በ"አይፐሲዜ" ውስጥ ቀርበዋል። "አይፐሲዜ"፤ ደራሲው ከአንጋፋዎቹ ደራሲዎቻችን ጋር በወጣትነት የማወቅ ጉጉት ያወጋውን እና አበክሮ ጠይቆ በማስተዋል የቀሰመውን የተረከበት፤ ከምስቅልቅል የማህበር ሕይወታችን ውስጥ የመዘዛቸውን እንከኖቻችንን የሔሰበት፤ በሕይወቱ አጋጥመውት የተደነቀባቸውን ሰዎችና ምልከታቸውን ያኖረበት፤... ሌሎችንም በተለመደው ድንቅ አቀራረቡ እና እንደ ምንጭ ውሃ ኮለል ብሎ በሚወርድ አተራረኩ ያቀረበበት ግሩም ሥራ ነው።

ባዩልኝ አያሌው
ገጣሚና የቋንቋ እና ሥነጽሑፍ መምህር

ISBN 978-99944-3-633-0

እታፍዘር አታሚዎች +25111 471 12 22

ዋጋው ብር 350 ብቻ
USD 10